ሰርጆች


ከበረደድ ገጿሙ



ደራሲ መምህር በረደድ ገዳሙ ከዚህ በፊት ሉባር በተሰኘ ተወዳጅ ድርሰቱ የምናውቀው ሲሆን አሁን ላይ ደግሞ የምስጢራት ሰረገላ የሆነውንና በርካታ የተደበቁ የሀገራችን ጥንታዊ ጥበብና ምስጢራትን ሳይንሳዊ በሆነ ቅኝት ፍለጋ የተካሄደበትን ሰርድዮን የተሰኘውን ሁለተኛ ድርሰቱን ይዞልን መጥቷል።

ደራሲው በሉባር የጀመረውን ረቂቅ ምስጢር ፍለጋ በሰርድዮን ወደ ዲማ ጊዮርጊስ ተመልሶ፦ ከዲማ ጊዮርጊስ እስከ ደብረ ገነት ሰይፍአጥራ ማርያም፤ ከደብረ ገነት ሰይፍአጥራ ማርያም እስከ ደጎማ ማርያም፤ ከደጎማ ማርያም እስከ አስመራ እንዳ ማርያም ብሎም እስከ ዳህላክ ደሴት በዘረጋው ተመራጭ መቼቱ ታሪክንና ምስጢርን በሚጣፍጥ ሁኔታ እንደዥረት አፍስሶ በመጨረሻም በግዮን ወንዝ አናት ላይ በአስደናቂ ሁኔታ ምስጢሩ እንዲፈታ አድርጓል።

ወጣት በረደድ በፕሮሰስ ምህንድስና የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቱን ያጠናቀቀ ሲሆን በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ተቋም ውስጥ በመምህርነት ሙያ እያገለገለ በተጓዳኝም አስተማሪና ሀገራዊ ለዛ ያላቸውን ድርሰቶች ለትውልድ እያበረከተ ይገኛል።



በገበያ ላይ

ሰርጀዮን

ከበረደድ ገዳሙ እሸቴ

✍ የደራሲው የቀደምት ስራ - ሉባር

©® በረደድ ገዳሙ እሸቱ- 1ኛ ዕትም 2014 ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
ALL RIGHTS RESERVED



ይህን መጽሐፍ ያለ ደራሲው ህጋዊ ፍቃድ በሙሉም ሆነ በከፊል በማንኛውም መንገድ ማባዛት፣ በኤሌክትሮኒክስ ውጤቶች መቅረፅና ማራባት፣ መገልበጥ እና ማሳተም እንዲሁም ወደ ፊልምና ተከታታይ ድራማ መቀየርም ሆነ ወደ ሌላ ቋንቋ ለመተርጎም መሞከር የቅጅና ተዛማጅ መብት ጥበቃ ጽ/ቤት ባወጣው አዋጅ ቁጥር 410/96 መሰረት በሕግ የተከለከለ ነው።



የኮምፒውተር ፅሁፍ - በረደድ ገዳሙ
የውስጥ ገፅ ቅንብር - ፀሐይ አስማማው

አድራሻ

Email- goldengedamu@gmail.com
Facebook Page – Bereded Gedamu
ባሕር ዳር /ኢትዮጵያ/

ቡክ ላንድ

አሳታሚና አከፋፋይ

+251- 922-74-02-02

+251- 930-08-33-08

ማስታወሻነቱ

ለውድ እናቴ ለወይዘሮ ገነት ስንታየሁ፤ ለውድ አባቴ ለአቶ ገዳሙ እሸቴ፤ እንዲሁም ስማችሁን ላልጠቀስኩት ሁሉም ቤተሰቦቼ እና ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትሉ በድርሰቱ ዓለም ውስጥ ሆናችሁ ጥበብን ለትውልድ ለማስተላለፍ ለምትጥሩት ሁሉ ይሁንልኝ።

ምስጋና

በቅድሚያ ይሀን ሰርድዮን የተባለውን በረቂቅ ምስጢራት ላይ ያተኮረውን ሁለተኛ መጽሐፌን እንዳጠናቅቅ የረዳኸኝ የጥበብ ሁሉ ምንጭና ባለቤት የሆንከው ልዑል እግዚአብሔር ከእናትህ ከቅድስት ድንግል ማርያም እና ከቅዱሳን ቤተሰቦችህ ጋር እስትንፋስ ባለው ፍጥረት ሁሉ ከምድር እስከ አርያም የተመሰገንህ ሁን።

በመቀጠል የማንነቴ መገለጫ፣ የፅናት፣ የፍቅርና የትዕግስት ተምሳሌት የማደርጋችሁ፤ ዘመናችሁን ሁሉ ስለ እኔ ሳሰስቱ ኖራችሁ ያሳያችሁኝ ውድ ወላጆቼ ለሁሉም ነገር መሰረቴ እናንተ ናችሁና ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ። በተጨማሪም የተገደፉ ፊደላትን በመልቀምና የሰዋሰው ስህተቶችን በማረም ይህ መጽሐፍ ለዚህ እንዲበቃ የረዳችሁኝ ወዳጆቼ፦ ዶ/ር ሞገስ ሚካኤል ከባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ የቋንቋ ት/ት ክፍል፣ መምህር ዲያቆን ውቤ እንግዳው፣ መምህር ተስፋ ነጋ፣ አቶ ገዳሙ መርሻ፣ አቶ አዲሱ አስፋው እና አቶ አየነው አዕምሮ ለትብብራችሁ ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ። በመጨረሻም በሀሳብ ስታበረታቱኝ የነበራችሁ፦ ዶ/ር መስፍን ወጋየሁ፣ ወ/ሮ ምንታምር ቀፀላ፣ መምህር ዮናስ ጎሳ፣ መምህርት ሐና ደርበው፣ ወ/ሪት ኢየሩሳሌም ለማ እና ስማችሁን ያልጠቀስኩት በርካታ ወዳጅ ጓደኞቼ ባላችሁበት ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ። ይህ ድርሰት የተጠበቀውን ያህል ሆኖ ካልተገኘ ተጠያቂው እኔ እንጅ ከላይ የተጠቀሱት ሰዎች እንዳልሆኑ ለማሳሰብ እወዳለሁ።

ማውጫ

መግቢያ 9

ምዕራፍ አንድ

ወደ ቅኔው መንደር 11

ምዕራፍ ሁለት

እማሆይ 21

ምዕራፍ ሦስት

ያልተነገረለት ኢትዮጵያዊው ሊቅ 31

ምዕራፍ አራት

ክስተት በሞጣ 41

ምዕራፍ አምስት

የጣሊያናዊው ማስታወሻ 49

ምዕራፍ ስድስት

በምድያም ምድር 55

ምዕራፍ ሰባት

የብራና ካርታ 63

ምዕራፍ ስምንት

ምስጢራዊው ዋሻ 71

ምዕራፍ ዘጠኝ

ጥበበኛው የቆሎ ተማሪ 77

ምዕራፍ አስር

አቡሻኽር 85

ምዕራፍ አስራ አንድ

የማክዳ ህልም በዲማ 93

ምዕራፍ አስራ ሁለት

ከሞት የተሰወሩት አባት 101

ምዕራፍ አስራ ሦስት

"ኢትዮጵያዊ መሆኔ በቂ ነው" 115

ምዕራፍ አስራ አራት

"በቸርቸል ጎዳና" 123

ምዕራፍ አስራ አምስት

የመልክዓ ምድር ሊቅ 133

ምዕራፍ አስራ ስድስት

"ዳግማዊት ምንትዋብ" 141

ምዕራፍ አስራ ሰባት

ፍለጋ በፎገራ 147

ምዕራፍ አስራ ስምንት

"የጥበብ ጥግ" 161

ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ

በደብረ ገነት ሰይፍአጥራ ማርያም 167

ምዕራፍ ሃያ 177

የልጅነት ትዝታ

ምዕራፍ ሃያ አንድ **197**

ጥልቁ ባሕር

ምዕራፍ ሃያ ሁለት 203

የጨለማው ንጉስ

ምዕራፍ ሃያ ሦስት 225

ምስጢራዊ ድንጋይ በደጎማ ማርያም

ምዕራፍ ሃያ አራት **235**

ቶጳዝዮን

ምዕራፍ ሃያ አምስት 245

ዳህላክ ደሴቱ ላይ

ምዕራፍ ሃያ ስድስት 265

ፍለጋ በግሽ አባይ

ምዕራፍ ሃያ ሰባት **275**

ምስጢሩ ሲፈታ

ምዕራፍ ሃያ ስምንት 283

ወደ ግዮን አናት

ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ 291

የሕይወት ዛፍ

መግቢያ

ይህ መጽሐፍ ሉባር ከተሰኘው ሰፋ ያለ ይዘት ካለው የመጀመሪያ ድርሰቴ በመቀጠል ለሁለተኛ ጊዜ ከአንባቢያን ጋር የተገናኘሁበት መጽሐፍ ነው። ድርሰቱ ከሉባር የቀጠለ ቢሆንም ራሱን ችሎ እንዲቆም ብዙ ጥረት ተደርጓል። ነገር ግን ይበልጥ የተሟላ መልዕክትና ሰፊ ግንዛቤ ለማግኘት ከፈለጉ ከሉባር ጀምረው ቢያነቡ ይመከራል። ሰርድዮን በዋነኛነት ሳይንስን ከሃይማኖት ጋር በማገናኘት የጥንት የአባቶቻችን የጥበብ ከፍታ በማሳየት እና በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ድብቅ ምስጢራትን በመግለፅ ላይ ያተኮረ ነው። ምንም እንኳ ድርሰቱ በይዘቱ መጠነኛ የልብ ወለድ አፃፃፍ ሂደትን ለመከተል ቢሞክርም በውስጡ የያዛቸው የሀሳብ ስብስቦች ግን ሊጨበጡና ሊዳሰሱ የሚችሉ በእውነት ላይ የተመሰረቱ ሀሳቦች ናቸው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ኢትዮጵያ ከዓለም ልዩ የሚያደርጋትን ዘመን ተሻጋሪ ረቂቅ ምስጢርና ጥበብ ሳይንሳዊ በሆነ አካሄድ ለመመርመር ጥረት ተደርጓል። በተጨማሪም አዳዲስ ያልተነኩ ታሪካዊና ምስጢራዊ ቦታዎችም ተዳስሰዋል። በድርሰቱ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ የቦታ አቀማመጥና ልኬት በእውነት ላይ የተመሰረተና ዘመኑ የደረሰበትን የቴክኖሎጅ ልኬት በመጠቀም የተረጋገጠ ነው። በጥቅሉ ጊዜ ወስዳችሁ ለመረዳት ከሞከራችሁ ሀገራችን ምን ያህል ለመመርመር የሚከብዱ የረቂቅ ምስጢራት ባለቤት እንደሆነች በቂ ግንዛቤ ታገኛላችሁ የሚል እምነት አለኝ። ምንም እንኳ ኢትዮጵያ ልዩና ጎበዕ የሆነች ሀገር ብትሆንም እኛ ግን አሁን ላይ ለእርሷ የሚመጥን ማንነት የሌለን ደካማ ትውልድ ሆነናል። ከዚህ አዘቅት ለመውጣት ማንነታችን ማወቅ፣ የንባብ ባህላችን ማዳበርና መንገዳችን ማስተካከል ይገባናል።

በሕይወታችን ውስጥ አንድ እርከን ከፍ ማለት ከፈለግን በንባብ የዳበረ እውቀትና ክህሎት ሊኖረን ይገባል። በንባብ ያልተገራ አዕምሮ ለመለወጥ ብቁ አይደለም ብዬ አስባለሁ። ምንም እንኳ እንደ ሀገር የንባብ ባህላችን በጣም ደካማ ቢሆንም ይህን ፈተና በመቋቋም አንባቢ ትውልድ በመፍጠር ሂደት ውስጥ የድርሻዬን ለመወጣት በምችለው ሁሉ ጥረት አደርጋለሁ። ታሪኩን የሚያውቅና የተሻለ ታሪክ የሚሰራ ጠንካራና ምክንያታዊ ማህበረሰብ በመፍጠር ከገባንበት አዙሪት ለመውጣት ሁላችንም ርብርብ ብናደርግ መልካም ይሆናል። ለቀጣይ ስራዎቼ ግብአት ይሆኑ ዘንድ ሀሳብና አስተያየቶቻችሁን በተጠቀሰው አድራሻ አድርሱኝ።

መልካም ንባብ!

✍ በረደድ ገዳሙ

ሰርድዮን



“ሰርድዮን የሉባር መጽሐፍ ቀጣይ ክፍል ነው። በዚህ ሰራ በሉባር የተጀመረው የጥንታዊ ገዳማትንና አድባራትን ምስጢራዊነት የመመርመር ሂደት ጎልቶ ይታያል። በጣና ሀይቅ፣ በደቡብና ሰሜን ጎንደር እንዲሁም በምስራቅና በምዕራብ ጎጃም ዞኖች የሚገኙ ጥንታዊ ገዳማት የሃይማኖት ማእከላት ብቻ ሳይሆኑ ለባህል፣ ለታሪክና ለሳይንስ እድገት መሰረት የሚሆኑ ምስጢራዊ ጉዳዮች መገኛዎች ስለመሆናቸውም በሰፊው ያትታል።

በአማርኛ ሥነጽሑፍ ታሪክ ራሳቸውን ችለው የተሟላ ሀሳብ ማስተላለፍ የሚችሉ የተለያዩ ድርሰቶችን በታሪክ በማስተሳሰር ማቅረብ በደራሲ ብርሃኑ ዘርይሁን ማእበሎች ተጀመረ እንጅ የቀጠለ አይመስለኝም። ሉባር እና ሰርድዮን እንደማእበሎች ናቸው።”

ዶ/ር ሞገስ ሚካኤል
በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ የዐባይ የቋንቋና የባህል ጥናት ተቋም ጎላፊ

‹‹ሰርድዮን በአባቶቻችን ጥንታዊ ጥበብ ላይ እንዲሁም በረቂቅና ጎቡዕ የኢትዮጵያ ምስጢራት ላይ በማተኮር ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሰፊ ዳሰሳ የተደረገበት ድንቅ መጽሐፍ ነው።

ደራሲው በድርሰቱ የሀገራችን የተሰወረ ጥንታዊ ረቂቅ ምስጢር ይገለጽ ዘንድ ዳገት ቁልቁለቱን ወጥቶና ወርዶ፤ በዱር በገደሉ ተንከራትቶ፤ ቁርና ፀሐዩ ሳይበግረው ስለከፈለው በዋጋ የማይተመን ጥረት ትውልዱ በቅብብሎሽ ሁሌም ሲያመሰግነው እንደሚኖር ሙሉ እምነት አለኝ።

በሰርድዮን ከዲማ ጊዮርጊስ የተሳበው ረቂቁ ምስጢር በግዮን ወንዝ አናት ላይ የተፈታበት መንገድ፤ ከአሁን በፊት ታሪክ ያልነካቸው ድንቅ ድንቅ ታሪካዊ ቦታዎች የተዳሰሱበት አግባብ፤ በሉባር የቴጌይቱ ምትክ፣ የጥበብና የውበት ማህደር ብሎ የሰየማት ተወዳጇ ማክዳ በዚህ ድርሰትም ተከስታ ከምስጢራዊ ቦታዎች በተጨማሪ እስከ አሰመራ፣ ምፅዋና ዳህላክ ደሴት ድረስ በመዘለቅ ከኤርትራዊቷ ፍዮሪና እና ከአብሮ አደጓ ማህሌት ጋር በመሆን ያደረጉት ልዩ ዳሰሳ ታሪኩ በልብ መቅረዝ ውስጥ ልዩ ቦታ ይዞ ዘመን እንዲሻገር ያደርጋል።

በጥቅሉ ሉባር እና ሰርድዮን ድንቅ የሥነፅሑፍ ለዛን የተላበሱ፣ በቀላል ቋንቋ ጥልቅ መልዕክትን የሚያስተላልፉ፣ ትውልድና ሀገርን ወደ ተሻለ ጎራ የሚያሻግር ሀሳብ የተንሸራሸረባቸው ስለሆነ ማንኛውም ማንበብ የሚችል ኢትዮጵያዊ ቢያነባቸው ከፍተኛ አውንታዊ አስተዋጽኦ የሚያሳድሩ ናቸው።››

(መምህር ዲያቆን ውቤ እንግዳው ከባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ)

BOOK LAND
0922740202

EIDO ADVERT

ዋጋ - 253.80 ብር